# ትራንስፖርት ባለስልጣን

## ያገለገሉ ተሸከርካሪ አስመጪዎች

## የተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀም

## መመሪያ ቁጥር 681/2013

መስከረም 2007

አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

አጭር ርዕስ

ነመሪያ የተሳላፊ ሠሌዳ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 681/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት የቃላት ትርጓሜዎች የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

ተሳላፊ ሠሌዳ" ማለት ማንኛውም ዓይነት ባለሞተር ወይም ተሳቢ ከደረቅ ወደብና ከጉሙርክ ፃቀረጪያ ጣቢያ ለማውጣት፤ ወደ ሽያጭ ቦታ ለማድረስ ወይም ከአስመጪው መጋዘን እስከ ፖርመራ ቦታ ድረስ ለማድረስ፤ እንዲሁም ተሽከርካሪው በ25 ኪሜ የደርሶ መልስ ርቀት ማስፈተሽ በጊዜያዊነት የሚሰጥ ሠሌዳ ነው፡፡

"ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የቋቋመ የትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡

የይለፍ መለያ ፈቃድ" ማለት ከተሽከርካሪ ጋር አብ ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ መለዋወጫ በስተቀር ሃንም ዓይነት ጭነት ሳይጭን ከጉሩምክ እስከ ተሽከርካሪው ማቆሚያ ብቻ ለመንቀሳቀስ ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

አግባብነት ያለው አካል" ማለት ባለስልጣኑ ወይም ሠሌዳውን ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ክልል ወይም የከተማ መስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ማለት ነው፡፡

አስመጪዎች" ማለት ማንኛውም ያገለገሉ ወይም አዲስ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ በማገባት ተሽከርካሪውን በመግዛትና በመሸጥ በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፡፡

የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች" ማለት ቋሚ ሠሌዳ ለመውስድ መረጃዎችን አሟልተው ጥያቄ ሚያቀርቡ ለተሽከርካሪ አስመጪዎች ወይም ግለሰቦች ተሳላፊ ሠሌዳ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

'ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

ማንናውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. አላማ

የተሳላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀምና አሰጣጥ ስርዓት ግልጽ ለማድረግና አጠቃቀምን አዋጅ ቁጥር 681/2002 በአንቀጽ 20-24 ለተጠቀሱት አላማዎች እንዲውል ለማቻል ነው፡፡

4. የመመሪያው ወሰን

ይህ መመሪያ የተሸከርካሪ አስመጪ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚጠቀሙበት ተሳላፊ ሠሌዳ ቁጥር የይለፍ መለያ ፈቃድ አጠቃቀምና አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የተለያዩ አካላት ትባርና ኃላፊነት

5. የትራንስፖርት ባለስልጣን ኃላፊነትና ተግባር

ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7/2/ረ መሰረት በተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሰሌዳዎችን ማምረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በተላላፊ ሠሌዳ አሰጣጥና አጠቃቀም ላይ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል

1. በአዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 15/2 እና 44 መሠረት አሁን በስራ ላይ ከዋለው /ካለው ኢት ሠሌዳ የተለየ መለያ ኮድ 'A' ፊደል ያለው እና ሚስጥራዊ ምልክቶች ያሉትን ሠሌዳዎችን ማምረት፤
2. ተሠጠው ተላላፊ ሠሌዳ በስራ ላይ ስለመኖሩና አለመኖሩ ቁጥጥርና ክትትል ማደረግ፤
3. የተሽከርካሪ አአስመጪነት ብቃት የማረጋገጫ ፈቃድ ለተሰጣቸው ድርጅቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ተላላፊ ሠሌዳ መስጠት፤
4. በተደጋጋሚ ተላላፊ ሠሌዳ በሚጥሉት እና ከመመሪያው ውጭ በሚጠቀሙት አስመጪ ድርጅቶች ላይ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በመመሪያው መሰረት ሕጋዊ ዕርምጃ መውሰድ፤
5. ተላላፊ ሠሌዳውን ለሚጠቀሙት ስለሠሌዳው አጠቃቀምና አሰጣጥ ምክርና ስልጠና መስጠት፤
6. ለሠሌዳ ጠያቂዎች ስለ ሠሌዳው አጠቃቀም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በማዘጋጀት ተላላፊ ሠሌዳ እንዲወስዱ ማድረግ፤
7. ከጉመሩክ መቅረጫ ጣቢያዎች በመገኘት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትን ተሽከርካሪዎች ወደ መቆሚያ ቦታቸው መድረስ የሚያስችል የይለፍ መንቀሳቀሻ ፈቃድ መስጠት፤
8. በዚህ መመሪያ አንጽ 9 የሚከናወኑ ቅጣቶች ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ ሪኮርድ በመያዝ እንዲሁም የቅጣት ክፊያውን በመሰብሰብ ተግባራዊነቱን በመከታተል ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

6. የአስመጪ ድርጅቶችና ግለሰቦች ኃላፊነትና ግዴታ

1. ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተላለፊ ሠሌዳ ጠያቂ ድርጅቶች የሚያስመጣቸውን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር በወሩ በተዘጋጀው ኢ-ሜይል አድራሻና በየ3 ወሩ በሀርድ ኮፒ በተዘጋጀው መሰረት ሪፖርቱን ለባለስልጣኑ የመላክ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. አስመጪ ድርጅቶች ባስመጣቸው ተሽከርካሪ ተላላፊ ሠሌዳ ከለጠፈ በኃላ የድርጅቱ ባለቤት ወይም የድርጅቱ ህጋዊ ተወካይ ብቻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ለተጠቀሱት ዓላማዎች እንድንቀሳቀስ ማድረግ፤
3. የተላላፊ ሠሌዳ የለጠፉ ተሽከርካሪዎች የምንቀሳቀሱት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ 12:30 እስከ ምሽቱ 1:30 ሲሆን ቅዳሜ ከጠዋቱ 12:30 እስከ 11:30 ሆኖ የሚጠቀመው ለማስፈተሽ፤ ወደ ጋራጅ፤ ወደ ማቆሚያ ቦታ ለማድረስ እና ወደ ትራንስፖርት ቢሮዎች ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ እሁድ ቀንና መንግስት የበዓላት ቀን ብሎ በሰየማቸው ቀናት አገልግሎት ላይ ማዋል አይቻልም፡፡

4. የተረከበው ተላላፊ ሠሌዳ ሲጠፋበት ምትክ ለማግኘት ከፖሊስና ስለመጥፋቱ ከፕረስ
ያሳወጀበትን ማስረጃ ካቀረበ በኋላ ለሦስት ወር እንዲቆይ ተደርጎ ለአንድ ሠሌዳ 500.00
/አምስት መቶ/ ብር በመክፈል ምትክ ተሰርቶ ይሰጠዋል:: ሁለቱ ከጠፋ ግን 1000.00
ብር በመክፈል የጠፋው ቁጥር እንዲመክን ተደርጎ ሌላ ሠሌዳ በማተም ይሰጠዋል::

5. የጠፋው ተላላፊ ሠሌዳ ሲገኝ ለባለሥልጣኑ ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ ተመላሽ
ማድረግ::

6. ስለተላላፊ ሠሌዳ አያያዝና አጠቃቀም በስሩ ላሉት ሠራተኞች ግንዛቤ መስጠት::

7. ማንኛውም ተላላፊ ሠሌዳ የወሰደ ድርጅት በመመሪያው መሰረት ባለሞተር ወይም ተሳቢ
ከደረቅ ወደብና ከጉሙሩክ መቅረጪያ ጣቢያ ለማስወጣት፣ ወደ ሽያጭ ቦታ ለማድረስ
ወይም ከአስመጪው መጋዘን እስከ ምርመራ ቦታ ድረስ ለማድረስ፣ እንዲሁም
ተሽከርካሪው በ25 ኪሜ የደርሶ መልስ ርቀት ለማስፈተሽ በጊዜያዊነት ከተቀመጠው ውጭ
ተሽከርካሪው ላይ በመለጠፍ ለግሉ ወይም ለድርጅት ስራ አገልግሎት መጠቀም
የተከለከለ ነው::

8. ተላለፊ ሠሌዳው ሲበላሽ ወይም ለዕይታ አስቸጋሪ ሲሆን ምትክ ሠሌዳ ማሰራት፣

9. ለተላላፊ ሠሌዳው ክፍያ በደንብ ቁጥር 206/2003 መሰረት ብር 250.00 /ሁለት መቶ
ሃምሳ ብር/ በእያንዳንዱ በሚወሰደው ሠሌዳ ክፍያ መፈጸም፣

10. የተላለፊ ሠሌዳ ተጠቃሚዎች ከሠሌዳው ጋር የሚሰጠውን የመንቀሳቀሻ ቅጽ
ተሽከርካሪውን በሚያንቀሳቅሱበት ወቅት ሞልተው መያዝ ይኖርባቸዋል::

11. እያንዳንዱ ተላላፊ ሠሌዳ ተጠቃሚ ድርጅት የአገልግሎት ጊዜው ካበቃ በኋላ ሠሌዳውን
ለሰጠው አካል ተመላሽ ማድረግ አለበት::

12. አስመጪ ድርጅት ለዕድሳት ሲመጡ ያስገቡትንና የሸጡትን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ
ዝርዝር መረጃዎችን በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው::

13. አንድ አስመጪ ድርጅት ለአስመጣቸው ተሽከርካሪዎች ለድርጅቱ ከተሰጠው ተላላፊ
ሠሌዳ ውጭ ለሌላ ድርጅት በተሰጠው ተላላፊ ሠሌዳ መገልገል አይቻልም::

## ክፍል ሦስት
## የተላለፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀምና ዕድሳት

7. ቋሚ ሠሌዳ ከትራንስፖርት ቢሮዎች ለመውሰድ የሚጠየቅ ተላለፊ ሠሌዳ
ከተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት ተገዝተው ወይም በተለያየ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ
አስገቢተው አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው ቋሚ ሠሌዳ ለማሰራት ትራንስፖርት
ቢሮዎች ድረስ ተሽከርካሪ ለማድረስ የሚጠይቅን ሰው በተመለከተ

1. ተሽከርካሪዎችን የሚመለከት ኢንቮይስ፣ ደከላራሲዮንና የማስገቢያ ፈቃድ
ኦርጅናል በመያዝ፣

2. ተላለፊ ሠሌዳ መውሰድ የሚችሉት ተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ
በሚያስመዘግቡት ትራንስፖርት የዞን ቢሮዎች ብቻ መሆን አለበት፣

3. ተሽከርካሪውን አስመዝግበው በሶስት ቀናት ውስጥ ተላላፊ ሠሌዳውን ተመላሽ
ማድረግ አለባቸው::

8. አዲስ ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅቶች ጊዜያዊ የኢት ሠሌዳ ለማግኘት ማቅረብ የሚገባቸው መረጃዎች

1. የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ ማቅረብ፤
2. ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪዎች ለዕድሳት በሚመጡበት ወቅት ከዚህ በፊት አንድ ዓመት ወደ ኋላ /ከሐምሌ 01 እስከ ሰኔ 30/ ያስመጡዋቸውን ተሽከርካሪዎች ብዛት ከአስር በላይ ከሆነ ዝርዝር በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት ሞልቶ በማቅረብ ለአንዴ ይታደስላቸዋል፤
   ሀ. ከሐምሌ 01 እስከ ሰኔ 30 ያመጡዋቸውን ተሽከርካሪዎች በሙሉ በቅጹ ላይ በመሙላት ከዲክላራሲዮን ኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት፤
   ለ. ከሐምሌ 01 እስከ ሰኔ 30 የሸጡዋቸውን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር በቅጹ ላይ በመሙላት ማቅረብ አለበት፤
   ሐ. በበጀት ዓመቱ ያልተሸጡ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር ከኦርጅናል ዲክላራሲዮን ወይም ሮዙን ወረቀት ኦርጅናሉንና ኮፒውን ማቅረብ አለበት፡፡
3. ከዚህ በላይ በመመሪያው አንቀጽ 8 (2) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያስመጡአቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት ከአስር ያልበለጡ ከሆነ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ በእጁ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር የያዘ በጉምሩክ ወይም በትራንስፖርት ቢሮዎች ዕርጥብ ማህተም የተረጋገጠ ዲክላራሲዮን ማቅረብ አለበት፡፡
4. የተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤
5. ባለቤቱ ከሆነ የታደሰ የቀበለ መታወቂያ ኮፒ ወይም የጸና ፓስፖርት ኮፒ ወይም ህጋዊ ወክል ከሆነ ውክልናና የታደሰ የቀበለ መታወቂያ ኮፒ፤
6. አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፊያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡


9. ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅቶች በሚያስመጡት ተሽከርካሪ መጠን የተላላፊ ሠሌዳ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል፤

1. በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ
   ሀ/ ከ31 እስከ 75 ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡት አስመጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል አንድ ተላላፊ ሠሌዳ፤
   ለ/ ከ76 እስከ አንድ መቶ ሃያ ለሚያስመጡ አስመጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሁለት ተላላፊ ሠሌዳ እና
   ሐ/ 121 በላይ ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡ አስመጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሦስት ተላላፊ ሠሌዳ፤
2. በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ21 እስከ 30 ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡት አስመጪዎች ለስድስት ወራት የሚያገለግል አንድ ተላላፊ ሠሌዳ፤

3. በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ11 እስከ 20 ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡት አስመጪዎች ለሦስት ወራት የሚያገለግል አንድ ተላላፊ ሠሌዳ፤
4. በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ 10 እና ከ10 በታች ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡ አስመጪዎች በአንድ ተሽከርካሪ ዲክላራሲዮን ለ1 ወር ብቻ የሚያገለግል አንድ ተላለፊ ሠሌዳ የሚሰጥ ሲሆን ማሳደስ የሚቻለው በሌላ ተሽከርካሪ ዲክላራሲዮን ብቻ ይሆናል፡፤በተመሳሳይ ዲክላራሲዮን ከአንድ ወር በላይ መውሰድ የተከለከለ ነው፡፡
5. በበጀት ዓመቱ ዕድሳት ሲያደርጉ በሚያስገቡት ተሽከርካሪ ብዛት የተላላፊ ሠሌዳ መቆያ ጊዜው ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

10. ስለ ዕድሳት

1. በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተላላፊ ሠሌዳ ለአንድ ዓመት የወሰደ አስመጪ ድርጅት የፍቃድ ጊዜው ሲያበቃ ለቀጣዩ ዓመት ማደስ የሚችለው በአንቀጽ 9 የተቀመጠውን መስፈርት ሲያሟላ ብቻ ነው፡፡
2. በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ተላላፊ ሠሌዳ ለስድስት ወር የወሰደ አስመጪ ድርጅት ፍቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በነበሩት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሰባት ያላነሱ ተሽከርካሪ ያስገባ ከሆነ ለ6 ወር ፍቃዱ ይታደስለታል፡፡ ሆኖም ከ7 ተሽከርካሪ በታች ያስገባ ከሆነ በአንቀጽ 9 ንዑስ 4 መሰረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡በተጨማሪም ለቀጣዩ ዓመት ፈቃዱን ማሳደስ የሚችለው በአንቀጽ 9 ላይ በተቀመጠው መስፈርት ብቻ ይሆናል፡፡
3. በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ተላለፊ ሠሌዳ ለሦስት ወር የወሰደ አስመጪ ድርጅት ፍቃዱን ከወሰደበት ጊዜው ጀምሮ በነበሩት ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከሦስት ያላነሱ ተሽከርካሪ ያስገባ ከሆነ ለ3 ወር ፍቃዱ ታደስለታል፡፡ ሆኖም ከ3 ተሽከርካሪ በታች ያስገባ ከሆነ በአንቀጽ 9 ንዑስ 4 መሰረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡በተጨማሪም ለቀጣዩ ዓመት ፈቃዱን ማሳደስ የሚችለው በአንቀጽ 9 ላይ በተቀመጠው መስፈርት ብቻ ይሆናል፡፡
4. በበጀት ዓመቱ ዕድሳት ሲያደርጉ በሚስያገቡት ተሽከርካሪ ብዛት የተላለፊ ሠሌዳ መቆያ ጊዜው በአንቀጽ 9 መሰረት ሊለዋወጥ ይችላል፡፡



# ክፍል አራት
## ልዩልዩ ድንጋገዎች

11. ክልከላ

1. ማንኛውም የተላላፊ ሠሌዳ ማንቀሳቀሻ ፈቃድ ተጠቃሚዎች በመመሪያው አንቀጽ 6(3) እና 6(7) ከተፈቀደላቸው የአገልግሎት መስጫ ጊዜ እና ቦታ ውጭ መጠቀም ክልክል ነው፤
2. ማንኛውም ተላላፊ ሰሌዳ ተሰጠው ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት ካስመጣቸው ተሽከርካሪዎች ውጪ አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን ማዋስ፤ መስጠትና ማከራየት የተከለከለ ነው፤
3. ማንኛውም ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት
   ሀ/ ከ31 እስከ 75 ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡት አስመ ጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል አንድ ተላላፊ ሠለዳ፤
   ለ/ ከ76 እስከ አንድ መቶ ሃያ ለሚያስመጡ አስመጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል
   ሁለት ተላላፊ ሠሌዳ እና
   ሐ/ 121 በላይ ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጡ አስመጪዎች ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሦስት ተላላፊ ሠሌዳ በላይ አይሰጣቸውም፡፡
4. ማንኛውም ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት ተላላፊ ሠሌዳውን በማይጠቀሙበት ጊዜ ተመላሽ ሳያደርጉ ማቆየት አይቻልም፤
5. ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት ከተሰጠው ተላላፊ ሠሌዳ ውጭ በሌላ ሠሌዳ መገልገል አይችልም፤
6. በአንድ ተላለፊ ሠሌዳ አንድ ድርጅት ብቻ የሚጠቀም በመሆኑ በዚህ በተላላፊ ሠሌዳ ለሚደርስ ችግር ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በማንኛውም ጊዜ ተላላፊ ሠሌዳ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ለሌላ አስመጪ ድርጅት አይሰጥም፡፡
7. ማንኛውም ተላላፊ ሠሌዳ የለጠፈ ተሽከርካሪ ግዥውን መፈጸም ከሚያስችለው ሰው ካልሆነ በስተቀር ሰውም ሆነ ዕቃ መጫን የተከለከለ ነው፡፡
8. ማንኛውም የተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት የተሰጠውን ተላላፊ ሠሌዳ በመለጠፍ በመመሪያው አንቀጽ 7 ከተሰጠው ተግባር ውጭ ለግል መጓጓዣም ሆነ ለድርጅት ስራ አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
9. ተላላፊ ሠሌዳ የለጠፈ ተሽከርካሪ በጋራጅ፤ በተሽከርካሪ ማሳያ ቦታ፤ በትራንስ ፖርት ቢሮዎችና ለፍተሻ በመንገድ ላይ ከሚንቀሳቀስ በስተቀር በሌሎች የከተማ ቦታዎች መንቀሳቀስ ወይም ማቆም የተከለከለ ነው፡
10. ማንኛውም የተላላፊ ሠሌዳ የለጠፈ ተሽከርካሪ የሚንቀሳቀሰው የትራንስፖርት ባለስልጣን ባዘጋጀው የመንቀሳቀሻ ሰነድ በመሙላት መሆን አለበት፡፡

12. ቅጣት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ላይ የተመለከተውን የተላላፊ ወይም የራሱ ያልሆነ ወይም በማስመሰል የተዘጋጀ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ለጥፎ ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ አሽከርካሪ ወይም ባለንብት በአዋጅ ቁጥር 68/2002 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን ይዞ በማቆየት በአዋጅ ቁጥር 68/2002 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በወንጀል በተደነገገው የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከብር 2500.00 እስከ ብር 5000.00 የሚደርስ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

| የጥፋቶች ዝርዝር | ቅጣት | መቀጮ |
|---|---|---|
| የተላለፊ ሠሌዳ የለጠፈ ተሽከርካሪ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 12:30 እስከ ምሽቱ 1:30 ሰዓት የሚንቀሳቀስ ሲሆን ቅዳሜ ከጠዋቱ 12:30 እስከ 11:30 ሆኖ የሚጠቀመው ለማስፈተሽ፤ ወደ ጋራጅ፤ ወደ ማቆሚያ ቦታ፤ ወደ ትራንስ ፖርት ቢሮዎች ብቻ ለማድረስ የሚያገለግል በመሆኑ እሁድ ቀንና የመንግስት በዓላት ቀናትን ሲገለገል ከተገኘ የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | የትራፊክ ተቆጣጣሪው ፖሊስ ጥፋት በፈጸመው የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ የቅጣት ወረቀት በመስጠት ተላላፊ ሠሌዳውን በመፍ ታት ለትራፊክ ጽ/ቤት ያስረክባል፡የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤ ትም ከትራፊክ ጽ/ቤት ሠሌዳውን ይሰበስባል፤ በተጨማሪም በአጥፊ ዎች ላይ በሚከተለው ሁኔታ ሪኮርዶችን የሚይዝ ይሆናል<br>1. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሪኮርድ በመያዝ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ለ6 ወር ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>4. ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት ሲፈጽም ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ይነጠቃል፡፡ | |
| የተሳሳተ ደክላራሲዮን መረጃ ያቀረበ አስመጪ ድርጅት ወይም አስመስሎ በተዘጋጀ የመንጃ ቅጽ ሲገለገል የተገኘ ግለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | የኢት ተላላፊ ለመውሰድ ያቀረበው ማስረጃ የተሳሳተ መሆኑ በባለስልጣኑ መ/ቤት ሲደረስበት ተላለፊ ሠሌዳውን ይነጠቃል | |
| የተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት የዕድሳት ጊዜውን አሳልፎ በቀረበ አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 1. ከ1 ቀን እስከ 90 ቀን ለእያንዳንዱ ቀን ቅዳሜንና እሁድን ጨምሮ 150.00 /መቶ ሃምሳ ብር ፤<br>2. ከ91 ቀን እስከ 180 ቀናት ያላሳደሰ ከሆነ በቀን 250 ብር እና ለሁለት ወር ዕግድ፤<br>3. ከ181 ቀን እስከ 270 በቀን 350 ብርና ለ4 /አራት/ ወር ዕግድ፤<br>4. ከ271 እስከ 360 ቀን በቀን 400 ብርና ስድስት ወር ዕግድ፤<br>5. ከ 361 ቀን በላይ በቀን 450 ብርና ለአንድ ዓመት ዕግድ ይጣልበታል | የተሽ/ሪ መለያ፤ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |

| የጥፋቶች ዝርዝር | ቅጣት | መቀጫ |
|---|---|---|
| ላላፊ ሠሌዳ ሲበላሽ ወይም ዕይታ አስቸጋሪ ሲሆን ምትክ ላለፊ ሠሌዳ ባልወሰደ አስመጪ ይም ግለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 500.00 /አምስት መቶ ብር በመክፈል ምትክ ተላላፊ ሰሌዳ እንዲወስድ ይደረጋል | የተሽ/ሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |
| ተላላፊ ሠሌዳ ተጠቃሚዎች ተላላፊ ሠሌዳ ጋር የሚሰጠውን መንቀሳቀሻ ቅጽ ተሽከርካሪውን ሚያንቀሳቅሱበት ወቅት ባልያዙ ተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 200.00 /ሁለት መቶ/ ብር ይቀጣል | የተሽ/ሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |
| ንድ አስመጪ ድርጅት ወይም ለሰብ ለአስመጣቸው ተሽከር ሪዎች ከተሰጠው ተላላፊ ሠሌዳ ሎጭ ለሌላ ድርጅት በተሰጠ ላለፊ ሠሌዳ ሲገለገል ከተገኘ ሚፈጸም ቅጣት | 1. ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ለመጀመሪያ ጊዜ 2500.00 /ሁለት ሺ አምስት መቶ/ ፤<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ 5000.00 /አምስት ሺ/ ብር የገንዘብ መቀጮ እና<br>3. ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ሠሌዳውን ይነጠቃል፡፡ | የተሽ/ሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |
| ተላላፊ ሰሌዳ የለጠፈ ተሽከ ካሪ በጋራጅ፤ በተሽከርካሪ ማሳያ ታ፤ በትራንስፖርት ቢሮዎችና ፍተሻ በመንገድ ላይ መንቀሳቀስ በስተቀር በሌሎች ከተማ መንገድና ቦታዎች ተሽከርካሪ አቁሞ ከተገኘ ሚፈጸም ቅጣት | የትራፊክ ተቆጣጣሪው ፖሊስ ጥፋት በፈጸመው የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ የቅጣት ወረቀት በመስጠት ተላለፊ ሰሌዳውን በመፍታት ለትራፊክ ጽ/ቤት ያስረክባል፡፡ የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤትም ከትራፊክ ጽ/ቤት ሠሌዳውን ይሰበስባል፡፡ በተጨማሪም በአጥፊዎች ላይ በሚከተለው ሁኔታ ሪኮርዶችን ይይዛል፡<br>1. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሪኮርድ በመያዝ የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ለ6 ወር ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>4. ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት ሲፈጽም ተላላፊ ሠሌዳ ማግኘት መብቱን ይነጠቃል፡፡ | የተሽ/ሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |
| የተረከበው ተላላፊ ሠሌዳ የጠፋበት ተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | በጋዜጣ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ወር እንዲቆይ ይደረግና<br>1. ነጠላ ሠሌዳ ከጣለ አምስት 500.00 በማስከፈል ምትክ ሠሌዳ ይሰጠዋል፤<br>2. ሁለቱንም የጣለ 1000.00 ብር በማስከፈል የቀድሞ ሠሌዳ እንዲመክን ይደረግና ሌላ ቁጥር ይሰጠዋል፡ | የተሽ/ሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 |

13.የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም አካል አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

14.ቅሬታ ስለማቅረብና ምላሽ ስለመስጠት

1. የተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ያልተስማማና ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በጽሑፍ በተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ለሚገኝ የቅርብ ኃላፊ ወይም ተጠሪ ማቅረብ ይችላል፤
2. አበቱታ የቀረበበት የክፍል ኃላፊ ወይም ተጠሪ ሁነታውን አጥንቶ አግባብ ያለውን ምላሽ በዕለቱ መስጠት አለበት፤
3. በመመሪያው አንቀጽ 14(2) ምላሽ የተሰጠው የአሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ በተሰጠው ምላሽ ካልተስማማ ቅሬታውን ለስነምግባር መከታተያና ቅሬታ ማስተናገጃ ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ቅሬታው የቀረበለት የስነምግባር መከታተያና ቅሬታ ማስተናገጃ ጽ/ቤት በሁለት ቀናት ውስጥ ምልሹን ያሳውቀዋል፡፡
5. የተሽከርካሪ አስመጪውም ግለሰብ በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማና ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለትራንስፖርት ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡
6. የትራንስፖርት ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ለቅሬታ አቅራቢው ምልሹን አቤቱታው በቀረበለት በ5 ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

15.መመሪያውን ስለማሻሻል

የባለስልጣኑ መ/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን ማሻሻል ይችላል፡፡

16.ተላላፊ ሠሌዳ ስለማግኘት

ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ድጅቶች ተላላፊ ሠሌዳ ለማግኘት የሚችሉት ከባለስልጣኑ መ/ቤት ብቻ ይሆናል፡፡

17.አገልግሎት የማይሰጡ ተላላፊ ሠሌዳዎች

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በስራ ላይ የነበሩ የቀድሞ ተላላፊ ሠሌዳዎች ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ አገልግሎት አይሰጡም፡፤

18.የመመሪያው አባሪ ሰነድ

የአስመጪዎች የግዴታ ማስገቢያ ፎርም 1 ገጽ

19.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ------------------ቀን ------------------ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

| ፉቶች ዝርዝር | ቅጣት |
|---|---|
| ሌፊ ሠሌዳ የለጠፈ ተሽከርካሪ ከሰኞ አርብ ከጠዋቱ 12:30 እስከ ምሽቱ ) ሰዓት የሚዝቀ ሳቀስ ሲሆን ቅዳሜ ዮቱ 12:30 እስከ 11:30 ሆኖ የሚጠቀ ለማስፈተሽ፣ ወደ ጋራጅ፣ ወደ ማቆ ቦታ፣ ወደ ትራንስ ፖርት ቢሮዎች ለማድረስ የሚያገለግል በመሆኑ እሁድ የመንግስት በዓላት ቀናትን ሲገለገል ኘ የሚፈጸም ቅጣት | የትራፊክ ተቆጣጣሪው ፖሊስ ጥፋት በፈጸመው የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ የቅጣት ወረቀት በመስጠት ተላላፊ ሠሌዳውን በመፍ ታት ለትራፊክ ጽ/ቤት ያስረክባል፡የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤትም ከትራፊክ ጽ/ቤት ሠሌዳውን ይሰበስባል፣ በተጨማሪም በአጥፊዎች ላይ በሚከተለው ሁኔታ ሪኮርዶችን የሚይዝ ይሆናል<br>1. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ለ6 ወር ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>4..ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት ሲፈጽም ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ይነጠቃል |
| ሳሳተ ደክላራሲዮን መረጃ ያቀረበ መጪ ድርጅት ወይም አስመስሎ ዘጋጀ የመንጃ ቅጽ ሲገለገል የተገኘ ሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | የኢት ተላላፊ ለመውሰድ ያቀረበው ማስረጃ የተሳሳተ መሆኑ በባለስልጣኑ መ/ቤት ሲደረስበት ተላለፊ ሠሌዳውን ይነጠቃል |
| ሽከርካሪ አስመጪ ድርጅት የዕድሳት ውን አሳልፎ በቀረበ አስመጪ ድርጅት ም ግለሰብ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 1. ከ1ቀን እስከ 90 ቀን ለእያንዳንዱ ቀን ቅዳሜንና እሁድን ጨምሮ 150.00 /መቶ ሃምሳ ብር ፤<br>2. ከ91 ቀን እስከ 180 ቀናት ያላሳደሰ ከሆነ በቀን 250 ብር እና ለሁለት ወር ዕግድ፤<br>3. ከ181 ቀን እስከ 270 በቀን 350 ብርና ለ4 /አራት/ ወር ዕግድ፤<br>4. ከ271 እስከ 360 ቀን በቀን 400 ብርና ስድስት ወር ዕግድ፤<br>5. ከ 361 ቀን በላይ በቀን 450 ብርና ለአንድ ዓመት ዕግድ ይጣልበታል |
| ላፊ ሠሌዳ ሲበላሽ ወይም ለዕይታ አስ ሪ ሲሆን ምትክ ተላለፊ ሠሌዳ ባልወሰ መጪ /ግለሰብ/ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 500.00 /አምስት መቶ ብር በመክፈል ምትክ ተላላፊ ሰሌዳ እንዲወስድ ይደረጋል |
| ላላፊ ሠሌዳ ተጠቃሚዎች ከተላላፊ ዳ ጋር የሚሰጠውን የመንቀሳቀሻ ቅጽ ሪውን በሚያንቀሳቅሱበት ወቅት ባልያዙ ሽ/ሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ ላይ ፈጸም ቅጣት | 200.00 /ሁለት መቶ/ ብር ይቀጣል |
| ድ አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስመጣቸው ተሽከር ካሪዎች ከተሰጠው ላፊ ሠሌዳ ውጭ ለሌላ ድርጅት ሰጠ ተላለፊ ሠሌዳ ሲገለገል ከተገኘ ፈጸም ቅጣት | ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ<br>1. ለመጀመሪያ ጊዜ 2500.00 /ሁለት ሺ አምስትመቶ/<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ 5000.00 /አምስት ሺ/ ብር የገንዘብ መቀጮ እና<br>3. ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ሠሌዳውን ይነጠቃል:: |
| ላላፊ ሰሌዳ የለጠፈ ተሽከ ርካሪ ራጅ፣ በተሽከርካሪ ማሳያ ቦታ፣ ራንስፖርት ቢሮዎችና ለፍተሻ ንገድ ላይ ከመንቀሳቀስ በስተቀር ሎች የከተማ መንገድና ቦታዎች ከርካሪ አቁሞ ከተገኘ የሚፈጸም ጣት | የትራፊክ ተቆጣጣሪው ፖሊስ ጥፋት በፈጸመው የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ የቅጣት ወረቀት በመስጠት ተላለፊ ሰሌዳውን በመፍታት ለትራፊክ ጽ/ቤት ያስረክባል:: የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤትም ከትራፊክ ጽ/ቤት ሠሌዳውን ይሰበስባል:: በተጨማሪም በአጥፊዎች ላይ በሚከተለው ሁኔታ ሪኮርዶችን ይይዛል፡<br>1. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሪኮርድ በመያዝ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ተላላፊ ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ለ6 ወር ሠሌዳ የማግኘት መብቱን ያጣል<br>4. ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት ሲፈጽም ተላላፊ ሠሌዳ ማግኘት መብቱን ይነጠቃል |
| ረከበው ተላላፊ ሠሌዳ የጠፋበት ሽከርካሪ አስመጪ ወይም ግለሰብ ላይ ፈጸም ቅጣት | በጋዜጣ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ወር እንዲቆይ ይደረግና<br>1. ነጠላ ሠሌዳ ከጣለ አምስት መቶ ብር በማስከፈል ምትክ ሠሌዳ ይሰጠዋል<br>2. ሁለቱንም የጣለ አንድ ሺ ብር በመክፈል የቀድሞ ሠሌዳ እንዲመክን ይደረግና ሌላ ቁጥር ይሰጠዋል፡ |
| ላፊ ሠሌዳ የተሰጠው የተሽ/ሪ አስመጪ ጅት ወይም ግለሰብ ለ3ኛ ወገን የሰጠ ራየ፤ ያዋስ ላይ የሚፈጸም ቅጣት | 1.ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ለመጀመሪያ ጊዜ 2500.00 /ሁለት ሺ አምስት መቶ<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ 5000.00 /አምስት ሺ/ ብር የገንዘብ መቀጮ እና<br>3. ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ሠሌዳውን ይነጠቃል:: |

ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪ ወይም ተላላፊ ሠሌዳ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀምመመሪያ ቁጥር 04/2007

## አባሪ የመንቀሳቀሻ ቅጽ

## የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን

መለያ ቁጥር 141/አዲ/ሰሌ/2006

ቀን ----------------------------

## ለአስመጪዎች ብቻ

## የተላላፊ/የዕለት/ ሠሌዳ ለማግኘት በአመልካቾች የሚገባ ግዴታ ቅጽ 12

. አመልካች ---------------------------------------- የተባልኩኝ የመኖሪያ አድራሻ ----------------
ፍለ ከተማ ቀበሌ/ወረዳ --------------- የቤት ቁጥር ------------ ስልክ ቁጥር -----------------
ዛሁት ተሽከርካሪ ምዝገባ ለማድረግ የተላላፊ ሠሌዳ አገልግሎት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡

አመልካች እኔ ከዚህ ጋር አባሪ ተደርጎ ባለው የጥያቄ ማቅረቢያ ማመልከቻ ቅጽ ሰረትየተፈቀደልኝን የተላላፊ ኢት መለያ ሠሌዳ ቁጥር ------------------ የተመዘገበውን ሬው ዕለት የተረከብኩኝ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 681/2002 የተዘረዘሩትን በሚገባ ተገንዝቤ ግንና ደንቡን አክብሬ ለመፈጸም የአገልግሎት ክፍያ ብር 250.00 /ሁለት መቶ ሃምሳ/ ንብ ቁጥር 206/2003 ፌጽሜ የተረከብኩ መሆኔን እያረጋገጥኩ፡-

የተሰጠኝኝ ሠሌዳ ሳልጥልና ሳላበላሽ በጥንቃቄ ለመያዝ፤
የተሰጠኝን ሠሌዳ በተሰጠኝ ጊዜ ውስጥ /ቀን/ ብቻ ተጠቅሜ ለመመለስ፤
የተሰጠኝን ሠሌዳ በማንኛውም ሕገወጥ ተግባር ላለማዋል ለሌላ አካል አሳልፌ ላለመስጠት
በሠሌዳው ከሰኞ  አርብ ከ12:30 — 1:30 እና ቅዳሜ ከ12:30 — 11:30 በስተቀር
በብሔራዊ በዓላት ቀን እንዲሁም ከከተማ ክልል ውጭ ላለማንቀሳቀስ /ላለመጠቀም;፤
በተሰጠኝ /በተፈቀደልኝ/ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተገልግዬ ለመመለስ፤
እንድገለገልበት ከተፈቀደልኝ አገልግሎት ውጭ ስጠቀም ብገኝ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ መሆኔን ተገንዝቤ በመፈረም የተፈቀደልኝን የተላላፊ ሠሌዳ የተሽከርካሪው ዓይነት በጠየቅኩት ላይ በመለጠፍ ለመንቀሳቀስ መረከቤን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ

መልካች ስም/ድርጅት ---------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ----------------
ዳን ያጣራው የተላላፊ ሠሌዳ መረጃ አጣሪና ፈቃጅ ሰራተኛ ስም --------------------------
ርማ ------------------
ሌዳውን የሰጠው የሠሌዳ መዝጋቢ ሰራተኛ ስም ------------------------ፊርማ ------------
የተሰጠው ሠሌዳ ቁጥር :- ----------------------------
የሠሌዳው መጠቀሚያ ጊዜ ከ ---------------- እስከ ---------------- ለ ----------- ቀን ብቻ
ሠሌዳው እንዲሰጥ ያረጋገጠው የኃላፊ ስም -----------------------------------------
ፊርማ --------------------------- ቀን -----------------------------------

ሳቢያ፡- የዚህ ግዴታ ውል ዋናው ከኦርጅናል ሰነዶች ጋር ይያያዛል፤ ኮፒው ለአመልካቹ ጣል፡

ያገለገሉ ተሽከርካሪ አስመጪዎች የተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀምመመሪያ ቁጥር 04/2007